# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት

## ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

## DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

## OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር 7
አርባምንጭ ታህሳስ 5 ቀን

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 7
Arbaminch December,


**አዋጅ ቁጥር 7/2016ዓ.ም**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ**

**መግቢያ**

የክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ተግባራቸውን ከማንኛውም ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖ ነፃ ሆነው በገለልተኛነትና በተጠያቂነት መንፈስ ማከናወን ያለባቸው በመሆኑ፤

የክልሉ ፍርድ ቤቶች ዳኞች እና የጉባዔ ተሿሚዎች ግልጽ፤ ገለልተኛና ተአማኒ በሆነ አሰራር የሚሾሙበትን ሥርዐት በመዘርጋት የፍርድ ቤቶችንና የዳኞች እንዲሁም የጉባዔ ተሿሚዎችን ብቃት፤ ነፃነት፤ ገለልተኝነትና ተጠያቂነት በማረጋገጥ የዳኝነት ሥርዓቱ የህግ

**Proclamation No. 7/2023**

**The Judicial Administration Proclamation of South Ethiopia Region**

**Preamble**

**WHEREAS,** Courts of the Region shall conduct their judicial functions in a spirit of impartiality and accountability, free from any internal or external influences;

**DETERMINED** to establish a judiciary that upholds the supremacy of the law and earns and maintains the trust of the people by ensuring transparency, impartiality and public confidence in the process by which judges are appointed as well as by ensuring that members of the judiciary conduct their judicial functions with complete

የበላይነትን ያስከበረ እና የሕዝብ አመኔታን ያገኘ እንዲሆን አስፈላጊ በመሆኑ፤

በክልል ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባዔና ንዑስ ጉባዔዎችን በየደረጃዉ በማዋቀር ተደራሽነትን ለማረጋገጥ፣ የጉባዔ አባላት ስብጥርና አመራረጥ ሥርዓት ግልፅና አሳታፊ በማድረግ ዉጤታማ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 7/2016 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) "ዋና ጉባዔ ወይም ጉባኤ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የክልሉ ዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ ነው፤

2) "ንዑስ ጉባዔ" ማለት በዚህ አዋጅ

independence, impartiality and accountability;

**WHEREAS**, it has become necessary to ensure accessibility by structuring the main and sub- Judicial Administration Council of the Region by making the composition and selection of members transparent and participatory to establish an effective working system,

**NOW THEREFORE,** the State Council of South Ethiopia Region, in accordance with Article 54 Sub-Article 3 of the Constitution has proclaimed this Proclamation.

## PART ONE

## MAIN PROVISIONS

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as ''South Ethiopia Region Judicial Administration Proclamation No. 7/2024."

2. **Definition**

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:-

1) "Main Council or Council" means the Region Judicial Administration Council established in accordance with this Proclamation;

2) "Sub-Council" means the sub-council

| | |
|---|---|
| መሠረት በጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የተቋቋመ ንዑስ ጉባዔ ነው፤ | established in accordance with this Proclamation by the supreme Court, and High Courts; |
| 3) “ጽሕፈት ቤት” ማለት የዋና ጉባዔ ወይም የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ነው፤ | 3) “Office” means the office of the main or Sub-Judical Council; |
| 4) “ሕገ-መንግሥት” ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ-መንግሥት ነው፤ | 4) “Constitution” means the Constitution of the South Ethiopia Region; |
| 5) “ፍርድ ቤት ወይም ፍርድ ቤቶች” ማለት እንደአግባብነቱ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የወረዳ ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማለት ነው፤ | 5) “Court or courts” means the Supreme Court, High Court, Wereda or City Court of First Instance of the Region, as the case may be; |
| 6) “ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት” ማለት ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ጨምሮ በየደረጃው ያለ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ነው፤ | 6) “President or vice president” means president or vice president of a Court at each level including the Supreme Court; |
| 7) “የጽሕፈት ቤት ኃላፊ” ማለት የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ወይም የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እንዲመራ የተሾመ ነው፤ | 7) “Head of office” means a person appointed to to manage the main or Sub-judicial Council; |
| 8) “ዳኛ” ማለት በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባዔ አቅራቢነት በክልሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ ዳኛ ነው፤ | 8) "Judge" means a judge appointed by the Regional State Council up on the Recommendation of the Regional Judicial Administration Council; |
| 9) “ደንብ” ማለት በዳኝነት አስተዳደር ዋና | 9) "Regulation" means the judicial code of Conduct and disciplinary procedures |

| | |
|---|---|
| ጉባዔ የፀደቀ የዳኞች ሥነ-ምግባርና የዲስፒሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብና ሌሎች በዚህ አዋጅ መሠረት በዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባዔ የሚዘጋጁ ደንቦችን ይጨምራል፤ | and other internal procedures enacted under this Proclamtion and approved by the Judicial Administration Council; |
| 10) "መመሪያ" ማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባኤ የሚወጣ ማንኛውም መመሪያ ነው፤ | 10) "Directive" means any directive enacted by the Regional Supreme Court and by Main Council; |
| 11) "ረዳት ዳኛ" ማለት በዳኝነት ስራ ዳኛን በማገዝ እንዲሰራ በጉባኤ የተሾመ የህግ ባለሙያ ነው። | 11) "Assistant Judge" means a legal professional appointed by the judicial council to assist judges; |
| 12)"ኮሚቴ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት በዋና ጉባዔ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤ | 12) "Committee" means a committee established by the Council in accordance with Article 10 of this Proclamation; |
| 13) "የኮሚቴ አባል" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 10 መሰረት በዋና ጉባዔው የተቋቋመ ኮሚቴ አባል ነው፤ | 13) "Committee member" means a member of a committee established by the Council; |
| 14) "የክልል ምክር ቤት" ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ነው፤ | 14) "State Council" means the South Ethiopia Region State Council; |
| 15) "የጉባዔ ተሿሚ" ማለት እንደአግባብነቱ በዋና ጉባዔ ወይም በንዑስ ጉባዔ የሚሾም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት | 15) "Appointee of the Judicial Administration Council" means the head of the office of the President of the Supreme Court, the head of the office of the judicial Council, the head of the office of the Public defender, the |

ኃላፊ፣ የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የአቤቱታ መስማት እና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪ፣ የምድብ ችሎት አስተባባሪ፣ ሬጅስትራር፣ ተከላካይ ጠበቃ፣ ወይም ቃዲ ሲሆን በዋና ጉባዔ ሆነ በንዑሳን ጉባዔዎች የሚሾሙ ሌሎች ሰዎችን ያጠቃልላል፤

16) "የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት" ማለት በዳኞች የሥነ-ምግባርና የዲስፕሊን ክስ ሥነ ሥርዓት ደንብ የስነ-ምግባር ጥሰት መሆኑ የተመለከተ ማናቸውም ድርጊት ነው፤
17) "ጉልህ የሥራ ችሎታ ማነስ" ማለት በዳኞች የሥነ-ምግባርና የዲስፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንብ የተመለከተ ድርጊት ሆኖ በዳኝነት ሥራ ላይ ሞያው ከሚጠይቀው የትምህርትና የልምድ ችሎታ በታች የሆነ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ስህተት መፈፀምን ይጨምራል፤
18) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ፍርድ ቤቶች፣ ዳኞች፣

head of the office of the sub-judicial council, the Coordinator of the Complaint Hearing and Decision Core process; the Division bench Coordinator, Registrar, Public Defender or Qadi and shall include other persons appointed by the Council and sub-Council;

16) "Judicial Misconduct" means any act that is recoginized as misconduct by the regulation on the judicial code of Conduct and disciplinary rule of procedure;
17) "Manifest incompetence " means an act which is specified in the regulation of the judicial code of conduct and rules of discipilinary procedure and includes committing an act or error below the competence and experience which the profession requires;
18) **"Person"** means a natural or juridical person;

**3. Scope of Application**

This Proclamation shall be applicable on the Regional Courts, Judges, appointees of judicial administration Council and presidents and Vice presidents as may be appropriate.

የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ተሿሚዎችና እንደአግባቡ ፕሬዚደንቶችና ምክትል ፕሬዚደንቶች ላይ ተፈጻሚ ነው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**የክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ መቋቋምና አደረጃጀት**

**4. መቋቋም**

1) የክልሉ ዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ፤ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ፤ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2) ዋና ጉባዔውም ሆነ ንዑስ ጉባዔው ቋሚ ጽሕፈት ቤት፣ ኃላፊ እና አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሯቸዋል፤
3) የጠቅላይ ንዑስ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ተጠሪነት ለዋና ጉባዔው ነው፤
4) የዋና ጉባዔ፣ የጠቅላይ ንዑስ ጉባዔ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ በጀት በየፍርድ ቤቶቻቸው ይመደባል፡፡

**5. የዋና ጉባዔ አባላት ስብጥር፤ አሰያየም እና የሥራ ዘመን**

1) የዋና ጉባዔ አባላት ስብጥር፡-

**PART TWO**

**Establishment, Organization, Powers and functions of the Regional Judicial Administration Council**

**Sub-Section One**

**Establishment and Organization of the Region Judicial Administration**

**4. Establishment**

1) The Regional Judicial Administration Council, Sub-council of the Supreme court, sub council of the regional high court, is hereby established by this Proclamation;
2) Main Council and Sub-council shall have regular office, head and necessary staffs;
3) The sub-council of the supreme and High Courts shall be accountable to the main Council;
4) Budjets of the main Council and sub-councils shall be allocated by each courts;

**5. Composition, Appointment and Tenure of the** Main **Council Members**

1) Composition of the members of the main Council:-
   a) The president of the Supreme Court-----

| | |
|---|---|
| ሀ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት…….. ሰብሳቢ፣ | ---------------------Chairperson; |
| ለ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት ….ምክትል ሰብሳቢ፣ | b) The Supreme Court Vice President … Vice Chairperson; |
| ሐ) ሁለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ………… አባላት፣ | c) Two Supreme Court Judge…..member; |
| መ) ሁለት የክልል ምክር ቤት አባላት በክልሉ ርዕስ መስተዳደር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሰየሙ ተመራጮች የምክር ቤት አመራርና የሕግ አስፈፃሚው አካል አባል ያልሆኑ (አንድ ወንድና አንድ ሴት) ……………. አባላት፣ | d) Two non high executive staff members from the State Council nominated by the State Council with consideration of both gender up on the approval of the President of the Region; |
| ሠ/ የክልል ፍትህ ቢሮ ኃላፊ…………... አባል | e) Head of Justice Bureau…… member; |
| ረ) ሁለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች …. አባላት | f) Two High Court judges…members; |
| ሰ) ሦስት የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች ……. አባላት | g) Three wereda court judge….members; |
| ሸ) የክልሉ ፍርድ ቤት ዳኞች ማኅበር ፕሬዚደንት…. አባል፣ | h) The Regional Judges Association President……. Member; |
| ቀ) የክልሉ ጠበቆች ማኅበር ፕሬዚደንት… …………አባል፣ | i) The Regional Bar Association President….Member; |
| በ) በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙ እዉቅና ካላቸዉ | j) One Law School Dean elected by the meeting of deans of law schools of recognized higher education institutions |

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የህግ ትምህርት ቤቶች ዲኖች የጋራ ስብሰባ የተመረጠ አንድ የሕግ ትምህርት ቤት ዲን……………………….አባል፤

ተ) የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን እና ቃዲዎችን የሚመለከት አጀንዳ ሲኖር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋና ቃዲ በአባልነት በድምጽ ይሳተፋል፤

ቸ) ተከላካይ ጠበቆችን የሚመለከት አጀንዳ ሲኖር የጠቅላይ ፍርድ ቤት የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በአባልነት በድምጽ ይሳተፋል፤

ኀ) ሌሎች የጉባዔ ተሿሚዎች የሚመለከት አጀንዳ ሲኖር አንድ የዋና ጉባዔ ተሿሚዎች ወኪል በአባልነት በድምጽ ይካፈላል፡፡

2) ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ጉባዔውን በሰብሳቢነት ይመራል፤

3) የዋና ጉባዔዉ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ኃላፊነታቸዉን ለመወጣት በማይችሉበት ጊዜ ዋና ጉባዔዉ አባል ከሆኑ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች መካከል አንዱን በጊዚያዊ ሰብሳቢነት በመሰየም ሥራዉን ሊያከናዉን ይችላል፡፡

4) የዋና ጉባዔ አባላት አስያየምና የሥራ

in the Regio…..member;

k) Where there is an agenda that concerns the Sharia Courts and Qadi, head of the Supreme Court Qadi shall participate with vote in the Council;

l) When there is an agenda that concerns for public defender, the head of the Office of the Public defender of the Supreme Court shall be voting participant of the Main Council;

m) When there is an ajenda that relates with other appointees, one delegate of main Council shall be voting participant;

2) In the absence of the chairperson, the Vice-President shall preside the Main Council;

3) When the Chairperson and Deputy Chairperson of the Main Council are incapable to fulfill their functions, one of the Supreme Court judges who are members of the Main Council may be appointed as the temporary chairperson.

4) Appointment and tenure of the members of the Main Council

a. The members of the Main Council referred to sub article (1) "c," "f," "g", this Article "m" of this Proclamation shall be appointed by election. Details

ዘመን

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (1) “ሐ”፣ “ረ” “ሰ” እና አንቀጽ ”ቸ” እና “ኀ” ድንጋጌዎች ሥር የተመለከቱት የዋና ጉባዔ አባላት በምርጫ ይሰየማሉ፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

ለ. የክልል ዋና ጉባዔ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዐስ አንቀጽ (1) “ሐ”፣ “ ሰ” ፣ “ረ” ፤ “ቸ” እና “ኀ” ድንጋጌዎች ሥር የተመለከቱት የዋና ጉባዔ አባላት በድጋሚ እንዲያገለግሉ ለአንድ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

<u>የክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

6. <u>የዋና ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

የክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የክልሉ የዳኝነት አገልግሎት የሚሻሻልበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤
2) የፍርድ ቤቶችና የዳኞች ነጻነትና ተጠያቂነት ሚዛናዊ እንዲሆን ይሰራል፤
3) የዳኞች ብቃት፣ መልካም ጠባይና ሥነ-ምግባር የሚዳብርበትን ተግባር ያከናውናል፤
4) የተገልጋዩ፣ የኅብረተሰቡና የመንግሥት

shall be determined by directive.

b. Tenure of the members of the Main Council referred to under the provisions, Article 5, sub article (1) “c” “f” “g” “l” and “m” of this Proclamation shall be five years, however, the member may be elected for one additional term.

**Sub Section Two**

**Powers and Functions of the Region Judicial Administration Council**

**6. Powers and Functions of the Main Council**

The Region Judicial Administration Main Council shall have the following powers and functions:-

1) Establish a system that improves the judiciary service in the region;
2) Works in the way that balance the independence and accountability of the courts and judges;
3) Performs the acts to develop the competency, good conducts and ethics of judges;
4) Follows-up and supports the implementation of a strategy to strengthen the satisfaction and trust of consumers, the community and the government;

| | |
|---|---|
| እርካታና አመኔታ የሚጠናከርበትን ስልት በመንደፍ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤ | |
| 5) ዋና ጉባዔዉ በአንቀጽ 10 መሠረት የተቋቋሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች የሚመሩበት ሥነ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፣ ኮሚቴዎች የተመደቡባቸዉን ኃላፊነት በብቃት መወጣታቸዉን ይቆጣጠራል፣ በየወቅቱም ይገመግማል፣ በግምገማዉ መሠረት ዉሳኔ ይሰጣል፤ | 5) The Main Council issues directive for the procedures to be conducted by the various committees established in accordance with Article 10; supervises the efficient performance of assigned responsibilities by committees, evaluates them periodically, and makes decisions based on the evaluation; |
| 6) በክልሉ ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ሙያ ለመሰማራት ብቁ ሆነው የተገኙ ዕጩ ዳኞችን ይለያል፡፡ ይሾሙ ዘንድም ለክልሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስተያየት ያቀርባል፤ | 6) Selects candidate judges who are competent to practice as a judge in the region courts. Submits suggestion to the Region Council of People's Representatives so that they can be appointed; |
| 7) የጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞችን ሹመት ለክልል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔን አስተያየት ይጠይቃል፤ | 7) Request the opinion of the Federal Judicial Council before submitting the nomination of judges of the Supreme and High Court to the Region People’s Representatives; |
| 8) የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የወረዳ ወይም የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞችን ሹመት ለክልል ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት ከሚመለከተው የዞን አስተዳደር ምክር ቤት አስተያየት ይጠይቃል፤ | 8) Request the opinion of the relevant zonal Administrative Council before submitting the candid judges of zonal or woreda or city administration judges to the State Council; |
| 9) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎት | 9) Decides the transfer of judges of the Supreme Court division bench judges and appointtees of main Council from one division bench to another, and of judges of |

| | |
|---|---|
| ዳኞችንና የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባዔ ተሿሚዎችን ከአንድ ምድብ ችሎት ወደ ሌላ ምድብ ችሎት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞችንና የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ተሿሚዎችን ከአንድ ዞን ወደ ሌላ ዞን የሥራ ቦታ ዝውውር ይወስናል፣ | the High Court and appointees of the judicial administration council from one zone to another zone. |
| 10) የዳኞችን፣ የዋና እና የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎችን፣ የተከላካይ ጠበቆችን፣ የረዳት ዳኞችን ደመወዝ፣ አበል፣ እረፍት፣ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን፣ ሕክምና፤ ደረጃና የዕድገት መሰላል እንዲሁም የፕሬዚደንቶችን እና ምክትል ፕሬዚደንቶችን ደመወዝና ጥቅማጥቅም አጥንቶ ይወስናል፡፡ | 10) Study and approve the salaries, allowances, vacancies, various benefits, ranks and promotions of the judges, Main and Sub-Council appointees; public defenders, and assistant judges as well as the salaries and benefits of presidents and vice presidents; |
| 11) የዳኞችንና የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ተሿሚዎችን በተመለከተ የሥነ-ምግባርና የዲሲፕሊን ደንብ ያወጣል፡፡ በሥራ ላይ እንዲዉል ያደርጋል፣ | 11) Regarding the judges and appointees' of judicial council, enact and apply administarative Regulation or a code of conduct and disciplinary rules; |
| 12) የዳኞችን፣ የዋና እና የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎችን የሥራ አፈጻጸም መመዘኛ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡ | 12) Establish and implement the performance appraisal system of judges, appointees of the main and sub-council; |
| 13) በክልሉ ፍርድ ቤቶች ዳኞች፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶችና ምክትል ፕሬዚደንቶች እንዲሁም በዋናም ሆነ በንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎች እንዲሁም በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚሰሩ | 13) Make decision when appeals are submitted on a charge of misconduct and disciplinary proceedings, manifest incompetence and inability to perform due to illness of judges of the courts, presidents and vice-presidents of the High Court as well as the nominees of the Main Council and the |

| | |
|---|---|
| ቃዲዎች ላይ የሚቀርቡ የሥነ ምግባርና የዲሲፕሊን ጥሰት ክሶችን፣ ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ ጉዳይን እና በህመም ምክንያት ሥራን ማከናወን አለመቻል ሁኔታን የሚቀርብለትን ይግባኝ ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል፤ | Sub-Council; |
| 14) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 እንደተመለከተዉ በንዑስ ጉባዔ ታይቶ ከሥራ እንዲሰናበት የውሳኔ ሀሳብ የቀረበበት ዳኛ ወይም ቃዲ ጉዳይ ዋና ጉባዔዉ መርምሮ በዲስፕሊን ጥሰት ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበት የቀረበዉን የዉሳኔ ሀሳብ ካፀና ዳኛዉን ከሥራ በማገድ ለመጨረሻ ዉሳኔ ለክልል ምክር ቤት ያቀርባል፡፡ ምክር ቤቱ የቀረበለትን የዉሳኔ ሀሳብ ተቀብሎ እንዲሰናበት ሲወስን ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ | 14) As stated in sub-article 12 of this article, the main Council shall examine the case of a judge or Qadi who has been considered by the sub-council and a proposal for his dismissal has been submitted to State Council, and when the council accepts the proposed resolution and decides to dismiss it, the judicial council accepts and implements it. |
| 15) ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ የታየባቸው፣ በሕመም ምክንያት ሥራቸውን ማከናወን ያልቻሉ ዳኞችን እና የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ተሿሚዎችን በሚመጥናቸው ሥራ ይመድባል፣ ስለሚከፈላቸው የደመወዝ መጠንም ይወስናል፣ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ አግባብ ባለዉ ህግ መሰረት ከሥራ ያሰናብታል፤ | 15) Judges and appointees of judicial council, who manifests incompetence and inefficiency, unable to perform their functions due to illness, shall be assigned to appropriate jobs; it determines the amount of wages paid to them, or dismisses them according to the relevant law as the case may be; |
| 16) በወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረን ዳኛ | 16) Remove immunity of judges suspected of criminal offences if it finds convincing |

| | |
|---|---|
| በተመለከተ የቀረበለትን ጥያቄ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው የዳኛውን ያለመከሰስ መብት ያነሳል፤ | evidence in a criminal case; |
| 17) የዓቢይ ጉባዔ ጽሕፈት ቤትም ሆነ የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት የሚመራበትን መመሪያ ያወጣል፣ ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፣ | 17) Issues a directive to the office of the main and Sub-Council; and follows-up its execution; |
| 18) በዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ረቂቅ ዓመታዊ የስራ ዕቅድ መርምሮ ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙንም ይገመግማል፤ | 18) Examine and approve the draft annual work plan and budget prepared by the office of the Main Council and evaluate its implementation; |
| 19) የዋና እና ንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤቶች የስራ አፈጻጸም መመሪያ በማውጣት ተፈጻሚ ያደርጋል፤ | 19) Issues and implements directrives for the work performance of the main and sub-council offices; |
| 20) የዋና ጉባዔም ሆነ የንዑስ ጉባዔ አባላት በሚሰበሰቡበት እና ለሥራ በሚሰማሩበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባውን የአበል መጠን ይወስናል፤ | 20) decides the amount of perduim to be paid to the members of the main council and the sub-council; |
| 21) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በወረዳ ፍርድ ቤት ደረጃ የሥነ-ምግባር ክትትል እና ኢንስፔክሽን ባለሙያ እንዲመደብ ደረጃውን ለይቶ ይወስናል፤ | 21) when it deems necessary, decides a supervision and inspection professional be assigned at the wereda court level; |
| 22) ክስ የቀረበበት ዳኛ ወይም የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ተሿሚ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በሥራ ላይ ቢቆይ በደል ያደርሳል ብሎ ያመነ እንደሆነ ደመወዙ እየተከፈለው ለጊዜው ከሥራ | 22) When it believes that the accused judge or the appointee of the Judicial Council, if the accused remains on duty may abuse the work, temporarily suspend from work until a decision has been made; |

| | |
|---|---|
| ታግዶ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፤ | |
| 23) የዲሲፕሊን ክስ በቀረበለት ጊዜ የተከራካሪ ወገኖችን እኩል የመሰማት መብት ያረጋግጣል፤ | 23) Ensures the right of parties to be heard equally at disciplinary proceedings; |
| 24) በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት አቅራቢነት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የአቤቱታ መስማትና መወሰን ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪን፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎት አስተባባሪን፣ በየደረጃው የሚገኙ የሸሪአ ፍርድ ቤት ቃዲዎችን፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤት ኃላፊን፣ የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ኃላፊን፣ የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት ኃላፊን እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ የሚሰሩ ተከላካይ ጠበቆችን፣የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰዉ ሀብት አስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊን እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ የሚሰሩ ሌሎች የጉባዔ ተሿሚዎችን ይሾማል፣ እንደአስፈላጊነቱም አግባብ ባለዉ ህግ መሰረት ከኃላፊነት ያነሳል፤ | 24) Appoints head of the office of the President of the Supreme Court, including the head of the office of the Main and the Region Sub-Counil of the Supreme Court, head of the Office of the public defenders and public defenders work at the level of the Suprme Court, Coordinators of the Appeal Hearing and Decision Core Process, Division bench Coordinators, Sharia Courts, Qadi at all levels, and other Council appointees and, as may be necessary; removes from his functions as may be necessary; |
| 25) የዳኞችን እና የጉባዔ ተሿሚዎችን የሥራ ቦታ ዝውውር ማስፈጸሚያ መመሪያ ያወጣል፡፡ | 25) Issues directives for the transfer of judges and council appointees. |
| 26) በሌሎች ህጎች የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡ | 26) Performs other functions provided by other laws. |

| | |
|---|---|
| 7. **<u>የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባዔ የይግባኝ ሥልጣን</u>**<br>በአንቀጽ 6 ከተደነገገው በተጨማሪ ዋና ጉባዔው የሚከተሉት የይግባኝ ሥልጣኖች ይኖሩታል፡- | 7. **The Appellate Power of the Judicial Administartion Main Council**<br>In addition to the provisions of Article 6, the Main Council shall have the following appellate powers:- |
| 1) በጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ በሥነ ምግባርና የዲስፕሊን ጥፋት ክሶች፣ ጉልህ የሥራ ችሎታ እና ቅልጥፍና ማነስ እና በሕመም ምክንያት ሥራን ማከናወን ያለመቻል ጉዳዮች ላይ የሰጣቸውን ውሳኔዎች ወይም የውሳኔ ሐሳቦችን በመቃወም የሚቀርቡ የይግባኝ ቅሬታዎችን መርምሮ እንደ አግባቡ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፡ | 1) Examines, appeals against the decision or recommendations of sub- councils over disciplinary offences, manifest incompetence and inefficiency and inability to perform work due to illness; |
| 2) በንዑስ ጉባዔ በሚሰጥ ሹመት፣ ከኃላፊነት የማንሳትና የዝውውር ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በይግባኝ መርምሮ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይሽራል፡፡ | 2) Examine, approves, amends, and revokes appeals against sub-councils decisions over transfer and removal from appointment; |
| 3) ከዳኝነት ሥራ ስንብት ውጭ ዋና ጉባዔው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤ | 3) Apart from the decision of removal from the judiciary, the decision of the Main Council in accordance with the provisions of this Proclamation shall be final; |
| 4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም ዋና ጉባዔው ከዳኝነት ማሰናበት ውጭ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሰጠው ውሳኔ የመሰማት መብትን በግልጽ የሚጥስ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ተፈጽሞብኛል የሚል ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ይህንኑ ለማሳረም ውሳኔው በተገለፀለት በ30 ቀን ውስጥ ይግባኙን ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት | 4) Notwithstanding the provisions of sub-article 3 of this article, any party claiming the right to be heared is apparently violated by Main Council decision, other than the dismissal of a judges, may appeal to the Regional Supreme Court within 30 days of the |

| | |
|---|---|
| ሊያቀርብ ይችላል። | decision is made. |
| **8. ይግባኝ ማለትን ማስታወቅና የይግባኝ አቤቱታን ማቅረብ** | **8. Noticing Appeal and Lodging Appeals Complaint** |
| 1) በንዑስ ጉባዔ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተገለፀለት በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማለቱን በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፤ | 1) A person who is aggrieved by a decision of a sub-council shall, within 15 days of the announcement of the decision, notify it in writing; |
| 2) የንዑስ ጉባዔው የጽሑፍ ማስታወቂያው በደረሰው በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ የተሰጠውን ውሳኔ ገልብጦ የመስጠት ግዴታ አለበት፤ | 2) The sub-council shall have a duty to give the copy of the decision within five working days of receiving the written notice to appeal; |
| 3) ይግባኝ ጠያቂው በንዑስ አንቀጽ 2 እንደተደነገገው የውሳኔ ግልባጭ በደረሰው ሣላሳ ቀናት ውስጥ የይግባኝ አቤቱታውን ከተሰጠው ግልባጭ ጋር ለዋና ጉባዔው ማቅረብ አለበት፤ | 3) The appellant shall submit to the Main Council within thirty days of receiving of a copy of the decision as provided in sub-article 2; |
| 4) በንዑስ አንቀጽ 2) እና 3) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፤ | 4) Appeals not submitted within the period specified in sub-articles 2) and 3) of this article shall not be admissible; |
| 5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4) የተጠቀሰው ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ባይ ምክንያቱ ካበቃበት በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን እንደየአግባቡ ለንዑስ ጉባዔ ወይም ለዋና ጉባዔ ሊያቀርብ ይችላል፣ የንዑስ ጉባዔ ወይም የዋና ጉባዔ ጊዜዉ | 5) Notwithstanding the provisions of sub-article 4 of this article, an appeal out time may be submitted to the sub-council or the main Council within ten working days of the end of the reason for force majeure; the decision of the sub-council or the main Council on appeal out of time shall be final. |

| | |
|---|---|
| ያለፈበት ይግባኝ አቤቱታ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ | |
| 9. <u>**የዋና ጉባዔ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር**</u> | **9. Powers and Functions of the Chairperson of the Main Council** |
| የጉባዔው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡- | Chairperson of the Council shall have the following powers and functions:- |
| 1) የዋና ጉባዔውን ጽሕፈት ቤት በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤ | 1) To manage and supervise principally the office of the Main Council; |
| 2) ከጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ጋር በመነጋገር የጉባዔውን የስብሰባ አጀንዳዎችን በማዘጋጀት ስብሰባ ይጠራል፣ አጀንዳዎችን ለጉባዔው ያቀርባል፣ ስብሰባውን ይመራል፤ | 2) To prepare and call to the council meeting agendas in consultation with the council Office ; to present agendas to the Council; to preside over the meeting; |
| 3) ለዳኝነትና ለዋና ጉባዔ ተሿሚነት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎችን ያሟሉ ዕጩዎችን ስም ዝርዝር ከአጭር የሕይወት ታሪክ መግለጫ ጋር አዘጋጅቶ ለዋና ጉባዔው ያቀርባል፤ | 3) To present to the Main Council the names of selected candidates that meet the criteria for admission to the Judiciary and the Main Council by preparing their short biography; |
| 4) በዋና ጉባዔው ተቀባይነት ያገኙ ዕጩ ዳኞች ዝርዝር ከአጭር ሕይወት ታሪክ መግለጫ ጋር ለክልል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለሹመት ያቀርባል፤ | 4) Present the list of candidates approved by the Main Council to the State Council with a brief biography; |
| 5) በሥራ ፍሰት አስገዳጅነት፣ የጤና ችግር ሲያጋጥም ወይም ያልተጠበቀ ነገር ሲከሰት ለዋና ጉባዔው ለውሳኔ በማቅረብ ዳኞችን በጊዜያዊነት አዛውሮ | 5) may temporarily transfer judges to the Main Council for a decision in the event of a compulsory workflow, health problems, or unexpected event; details shall be determined by the directive; |

| | |
|---|---|
| ሊያሰራ ይችላል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤<br>6) ዋና ጉባዔውን የተመለከቱ ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል፡፡<br>10. <u>የዋና ጉባዔው ኮሚቴዎች</u><br>1) ዋናው ጉባዔ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ያመቸው ዘንድ ለውሳኔ መነሻ የሚሆኑ ጉዳዮችን አጥንተው የሚያቀርቡና እያንዳንዳቸው ከ3 (ሶስት) እስከ 5 (አምስት) የሚደርሱ የዋና ጉባዔ አባላት ወይም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሰዎች የሚመደቡባቸው እንደ ሁኔታው በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የሚሰሩ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡-<br>ሀ) የዳኞችና የዋና ጉባዔ ተሿሚዎች ምልመላ፣ ሹመት፣ ዕድገትና ዝውውር ኮሚቴ፣<br>ለ) የሥነ-ምግባርና ዲሲፕሊን ኮሚቴ፣<br>ሐ) የበጀት፣ የፋይናንስ፣ የደመወዝ፣ የአበልና ጥቅማጥቅም ኮሚቴ፣<br>መ) የሰው ሀብት፣ ትምህርትና ሥልጠና ጉዳይ ኮሚቴ፤<br>2) የኮሚቴ አባላት፣ ስብጥር፣ አመራረጥና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ዋና ጉባዔ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡ | 6) Performs other related activities related to the Main Council.<br>**10. Committees of the Main Council**<br>1) The Main Council shall have permanent or interim committees, that enables it to be competent to carry out the functions and responsibilities assigned to it by this Proclamation, which shall be appointed by the Main Council or any other relevant persons, each of whom shall appoint 3 (three) to five (5) members of the Main Council or other relevant persons, to study the issues that are the basis for the decision:-<br>a) Recruitment, appointment, promotion and transfer committee of judges and appointees of the Main Council;<br>b) Ethics and Discipline Committee;<br>c) Budget, Finance, Salary, Allowance and Benefits Committee;<br>d) Human Resource, Education and Training Affairs Committee;<br>2) Composition, selection, and work procedure of committee members shall be determined by a directive to be issued by the main Council. |

| | |
|---|---|
| 11.<u>የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ አባላት</u><br>1) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ተጠሪነቱ ለዋና ጉባዔ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦<br>ሀ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ መስማት እና መወሰን ዋና ሥራ ሂደት ባለቤት ሰብሳቢ፤<br>ለ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች በጋራ የሚመርጧቸው ሁለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ከእነዚህም መካከል ቢያንስ አንድ ሴት ብትሆን ይመረጣል፡፡ ከሁለቱ የንዑስ ጉባዔ አባል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች መካከል በዋና ጉባዔዉ የሚሰየም አንድ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የንዑስ ጉባዔ ምክትል ሰብሳቢ ይሆናል፤<br>ሐ) ሁለት የክልል ምክር ቤት አባላት በክልሉ ርዕስ መስተዳደር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሰየሙ ተመራጮች የምክር ቤት አመራርና የሕግ አስፈፃሚው አካል አባል ያልሆኑ፤<br>መ/ የክልል ፍትህ ቢሮ ምክትል ኃላፊዎች መካከል በቢሮ ኃላፊ የሚወከል አንድ ምክትል ኃላፊ አባል፤<br>ሠ)የጠቅላይ ፍርድ ቤት የጉባዔ | **11. Members of the Supreme Court Sub-Council**<br>1) Sub-Council of the supreme court shall be accountable to the main Council and shall have the following members:-<br>a) Complaint Hearing and Decision Core Process Owner of the Supreme Court shall be chairperson;<br>b) Two judges elected from Supreme Court and one from among them should be female. One judge of supreme court who is elected from two sub council members of the supreme court assigned by the main Council shall be vice chairperson of the sub-council;<br>c) Two members of the State Council who are elected by the State Council up on the recommendation of the Chief Executive of the Region, who are not higher officials and members of the executive body;<br>d) One representative member from among the deputy heads of the Regional Justice Bureau assigned by Head of Justice Bureau;<br>e) One representative member jointly elected by the Supreme Court |

| | |
|---|---|
| ተሿሚዎች በጋራ የሚመርጡት አንድ ተወካይ አባል፤ | appointees; |
| ረ) አንድ የክልል ዳኞች ማኅበር ተወካይ አባል፤ | f) One representative from the Regional Judges' Association…. member; |
| ሰ) አንድ የክልል ጠበቆች ማኅበር ተወካይ አባል፤ | g) One representative from the Regional Bar Association; |
| ሸ) አንድ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት በዋና ጉባዔ አባል ያልሆነ፤ | h) One elected from presidents of High Courts who is not a member of the Main Council; |
| ቀ) በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ከዳኝነት አስተዳደር ጽህፈት ቤት የሚሰየም ድምጽ የማይሰጥ ፀሀፊ | i) A secretariat appointed by the President of the Supreme Court from Judicial Administration staffs having no vote; |
| 2) የየጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ አባል ሆኖ የሚመረጥ ዳኛ በሥነ-ምግባር አርዓያ የሆነ፣ ከፍተኛ የሥራ አፈጻጸምና ልምድ ያለው መሆን አለበት፤ | 2) A judge elected as a member of sub council shall be exemplary in his conduct, have high work performance and experience; |
| 3) ቃዲን የሚመለከት ጉዳይ ሲኖር በዋና ቃዲ የሚወከል አንድ ቃዲ በንዑስ ጉባዔው ስብሰባ ላይ በድምጽ ይሳተፋል፤ | 3) When there is an issue with regard to a Qadi, a Qadi representing the Chief Qadi shall participate with vote in a sub-council; |
| 4) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ አባላት የሚሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚደንቶች ይመረጣሉ፤ | 4) The Presidents of the High Courts, who are to be members of the supreme court Sub-Council, shall be elected by the Presidents of the High Courts; |
| 5) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ አባል የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1) /ለ/ እና | 5) Tenure of a member of the Supreme Court sub-council shall be five years; however, members elected in |

| | |
|---|---|
| /ሐ/ መሰረት የተመረጡ አባላት በድጋሚ እንዲያገለግሉ ለአንድ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ | accordance with sub-article 1) b) and c) of this article, may be re-elected for one additional time. |
| 12.**<u>የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>**<br>የየጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡- | **12. Powers and Functions of the Supreme Court Sub-Council**<br>The Supreme Court Sub-Council shall have the following powers and functions:- |
| 1) በጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ያሉ የጉባዔ ተሿሚዎች፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶች፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤትና በወረዳ ፍርድ ቤት ቃዲዎች ላይ የሚቀርብ የሥነ-ምግባር ጥሰትና የዲስፕሊን ክሶችን፣ ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ ጉዳይንና በህመም ምክንያት ሥራን መሥራት አለመቻል ሁኔታን ተመልክቶ እንደአግባብነቱ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ ይሰጣል፤ | 1) Passes decision or gives recommendation as may be necessary on the Supreme Court judge, appointees on rank of the Supreme Court, the High Court and Weredas Court Qadis, on cases of misconduct and disciplinary charges brought on manifest incompetence and inefficiency and inablity to work due to illness; |
| 2) የሥነ-ምግባር ጉዳይን አስመልክቶ በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ተጨማሪ ሥራ ይሰራል፡፡ | 2) Performs additional functions assigned by the President on matters of code of conduct. |
| 13.**<u>የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር</u>**<br>የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ሰብሳቢ ተጠሪነት ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡- | **13. Powers and Functions of the Chairperson of Supreme Court Sub-Council**<br>The chairperson of the Supreme Court Sub-Council shall be accountable to the President |

1) የንዑስ ጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፤
2) የሥነ-ምግባር ጉዳዮችን ተቀብሎ ለንዑስ ጉባዔው ያቀርባል፤
3) የንዑስ ጉባዔውን ሥራ አደራጅቶ ይይዛል፣ የሥነ-ምግባር መረጃን ያጠናክራል፣ ይይዛል፤
4) የንዑስ ጉባዔውን መዛግብትንና ሰነድ በአግባቡና በዘመነ መልኩ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤
5) የንዑስ ጉባዔውን ሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ ዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፤
6) በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**14.<u>የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ አባላት ስብጥር፤ አሰያየም እና የሥራ ዘመን</u>**

1) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ተጠሪነቱ ለዋናዉ ጉባዔ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ሰብሳቢ፣

ለ) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት ምክትል ሰብሳቢ፣

ሐ) ሁለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች (ጾታን አካታች የሆነ)

and shall have the following powers and functions:-

1) Convenes and presides over the meeting of the sub-council;
2) Receives and submits ethical issues to the sub-council;
3) Organizes and holds the work of the sub-council, strengthens and maintains ethical information;
4) Ensures that the sub-council records and documents are maintained properly and up-to-date;
5) Prepare the performance report of the sub-council and submit it to the Office of the Main Council;
6) Performs other functions assigned to it by the President.

**14. Composition, appointment and Tenure of the High Court Sub-Council Members**

1) sub-council of the High Courts shall be accountable to the main Council and have the following members:-

a) President of the High Court…Chair person;

b) Vice President of the High Court…. Vice chair person;

c) Two members of the High Court judges

| | |
|---|---|
| | (gender inclusive) …….member; |
| መ) አንድ የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት | d) One Wereda Court President ….. member; |
| ሠ) ሁለት የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች (ጾታን አካታች የሆነ) | e) Two Wereda court judges (gender inclusive) …….member; |
| ረ) ከዞን ምክር ቤት የሚወከሉ ሁለት አባላት፣ | f) Two representatives from the zonal council members ……. member; |
| ሰ) የከፍተኛና የወረዳ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን እና ቃዲዎችን የሚመለከት አጀንዳ ሲኖር የከፍተኛ ፍርድ ቤት ቃዲ በድምጽ በንዑስ ጉባዔው ላይ ይካፈላል፤ | g) When there is an agenda concerning high and wereda Shariah courts and Qadis, the Qadi of the High Court shall participate with a vote; |
| ሸ) በከፍተኛም ሆነ በወረዳ ደረጃ የሚሰሩ ተከላካይ ጠበቆችን የሚመለከት አጀንዳ ሲኖር በዚሁ ደረጃ ከሚሰሩ ተከላካይ ጠበቆች አንድ ተወካይ ተከላካይ ጠበቃ በድምጽ በንዑስ ጉባዔው ላይ ይሳተፋል፤ | h) When there is an agenda concerning public defenders working at the high or wereda level, one representative public defender from public defense working on this level shall be voting participant in the sub-council; |
| ቀ) ሌሎች የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎችን የሚመለከት አጀንዳ ሲኖር አንድ የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎች ወኪል በአባልነት በድምጽ ይሳተፋል፤ | i) When there is an agenda concerning other appointees of Sub-Council, one representative of the appointees of the Sub-Council shall participate in voting as a member; |
| በ) ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ንዑስ ጉባዔውን በሰብሳቢነት ይመራል፤ | j) In the absence of the Chairperson, the Vice-President shall preside over the Sub-council as Chairperson; |
| 2) የንዑስ ጉባዔ አባላት አስያየምና የሥራ ዘመን | 2) Appointment and tenure of members of the Sub-Council |
| ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ንዐስ አንቀጽ | a. The members of the Sub-Council referred |

| | |
|---|---|
| (1) “ሐ”፣ “መ”፣ “ሠ” ድንጋጌዎች ሥር የተመለከቱት የንዑስ ጉባዔ አባላት በምርጫ ይሰየማሉ፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡ | to in the provisions of Article 14, sub article (1), "c," "d," and "e" of this proclamation shall be appointed by election. Details shall be determined by directive. |
| ለ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (1) “ሐ”፣ “መ” ፣ “ሠ” ፤ ረ ድንጋጌዎች ሥር የተመለከቱት የንዑስ ጉባዔ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ማንኛውም አባል ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን በድጋሚ ከመመረጥ አይከለከልም፡፡ | b. Tenure of the Sub-Council members shall be five years according to Article 14 this proclamation, sub Article (1) "c," "d", " “e” and “f.“ However, no member shall be barred from re-election for one additional term. |
| 15. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር | **15. Powers and Functions of the Sub-Council of the High Court** |
| 1. በንዑስ ጉባዔው ጽሕፈት ቤት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን ረቂቅ ዓመታዊ የስራ ዕቅድ ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙንም ይገመግማል፤ | 1) Examine and approve the draft annual work plan and implementation budget prepared by the sub-council Office and evaluate its implementation; |
| 2. ለከፍተኛና ለወረዳ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞችን በምልመላና መረጣ መመሪያ መሠረት መርጦ ለክልሉ ዋና ጉባዔ ያቀርባል፤ | 2) Selects and submits judges for the High and Woreda Courts in accordance with the recruitment and selection directive; |
| 3) በከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት አቅራቢነት የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ኃላፊን፣ የከፍተኛና የወረዳ ፍርድ ቤት የአቤቱታ መስማትና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችን፣ ሬጅስትራሮችን፣ | 3) Appoints head of the Office of the Sub-Council, the Coordinators of the Complaint Hearing and Decisioon Core Process of the High Court and wereda court; the Division bench Coordinator, Registrar, Defense Attorney; removes from their position as |

| | |
|---|---|
| የምድብ ችሎት አስተባባሪዎችን፣ ተከላካይ ጠበቆችን እና ሌሎች የጉባዔ ተሿሚዎችን ይሾማል፣ እንዳስፈላጊነቱም ከኃላፊነት ያነሳል፤ | may be necessary; |
| 4) በከፍተኛና በወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ በንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎች እንዲሁም በከፍተኛና በወረዳ ፍርድ ቤት ቃዲዎች ላይ የሚቀርቡ የሥነ-ምግባር ጥሰትና የዲሲፕሊን ክሶችን፣ ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ ጉዳይንና በህመም ምክንያት ሥራን መሥራት አለመቻል ሁኔታን ተመልክቶ እንደአግባብነቱ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ ይሰጣል፤ | 4) Make decision or provides recommendations on a charge of misconduct and disciplinary proceedings, manifest incompetence and inability to perform due to illness against judges of the High and Wereda courts as well as on the High and and wereda Courts Qadis as may be appropriate; |
| 5) በዞኑ ውስጥ ከአንድ ወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ወረዳ ፍርድ ቤት የሚደረግ የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞችን፣ ቃዲዎችንና ሌሎች የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎችን ዝውውር ተመልክቶ ይወስናል፤ | 5) Decide on the transfer of judges, Qadi and other sub-council appointees from one Wereda court to another Wereda court in the same zone; |
| 6) የዳኞች እና የጉባዔ ተሿሚዎችን የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ በመመሪያው መሰረት አዘጋጅቶ ለክልሉ ጉባዔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤ | 6) Study the promotion of judges and appointees of the Council to the Region council and implement upon its approval; |
| 7) በዳኞችና በንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎች ላይ በዋናው ጉባዔ የሚሰጡ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን ተከታትሎ ያስፈጽማል፤ | 7) Follow up and enforce various decisions made by the Main Council on judges and sub-council appointees; |

| | |
|---|---|
| 8) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሰረት ለዋናው ጉባዔ ከተሰጡ ስልጣንና ተግባራት መካከል እንደስራው ባህርይ አስፈላጊ የሆኑትን በስራ ላይ ያውላል፤ | 8) Implement among the powers and functions assigned to the Main Council in accordance with Article 6 of this Proclamation, which are necessary in the nature of the work; |
| 9) በዋና ጉባዔው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል። | 9) Performs other functions assigned to it by the Main Council. |
| **16.<u>የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር</u>** | **16. Powers and Functions of the Chairperson of the Sub-Council of the high court** |
| የንዑስ ጉባዔው ሰብሳቢ፡- | Chairperson of the Sub-Council:- |
| 1) የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤ | 1) Supervise, administer and leads the Office of the sub-council; |
| 2) ከጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ጋር በመነጋገር የስብሰባ አጀንዳዎችን አዘጋጅቶ ስብሰባ ይጠራል፣ ስብሰባውንም ይመራል፤ | 2) In consultation with the head of the Office, prepare a meeting agenda and presides a meeting; |
| 3) በንዑስ ጉባዔ የስራ መደብ የተሿሚነት መመዘኛዎችን ያሟላ ዕጩን ስም ዝርዝር ከአጭር የሕይወት ታሪክ መግለጫ ጋር አዘጋጅቶ ለንዑስ ጉባዔው ያቀርባል፤ | 3) Prepare a list of candidates who meet the criteria for appointment in the sub-council with a brief biography and submit it to the sub-council; |
| 4) በሥራ ፍሰት አስገዳጅነት፣ የጤና ችግር ሲያጋጥም ወይም ያልተጠበቀ ነገር ሲከሰት ለንዑስ ጉባዔው ለውሳኔ በማቅረብ ዳኞችን በጊዜያዊነት አዛውሮ ሊያሰራ ይችላል፣ ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤ | 4) May temporarily transfer judges to the sub Council for a decision in the event of a compulsory workflow, health problems, or unexpected event; details shall be determined by the directive to be issued by the Supreme Court; |

5) ሌሎች ንዑስ ጉባዔውን የሚመለከቱ ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሶስት

## የጉባዔዎች የውሳኔ አሰጣጥ፣ የስብሰባ ጊዜና ሥነ-ሥርዓት

### 17.የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

1) ዋና ጉባዔውም ሆነ ንዑስ ጉባዔዎች በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋሉ፣ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠሩ ይችላሉ፤

2) ከአባላት መካከል ሁለት-ሦስተኛ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

3) በዚህ አዋጅ በዋና ጉባዔ ወይም በንዑስ ጉባዔ በልዩ ሁኔታ ድምጽ እንዲሰጥባቸው የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ በዋና ጉባዔው ወይም በንዑስ ጉባዔው በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ፣ ሆኖም ድምጽ እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

4) የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም የዋና ጉባዔ ወይም ንዑስ ጉባዔ አባል የራሱ ወይም የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዱ ጉዳይ ታይቶ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ የቀረበበትን ዲስፕሊን የሚመለከት የዋና ጉባዔ ወይም ንዑስ ጉባዔ ጠቅላላ ስብሰባም ሆነ በተመደበበት ኮሚቴ ላይ

5) Performs other related activities related to the sub-council.

## Sub Section Three

## Decision making, meeting time and Procedure of the Councils

### 17. Meeting Procedure

1) The Main Council and the sub-Council shall hold a regular meeting once a month; it may convene an extraordinary meeting at any time as may be necessary;

2) A quorum shall be held when two-thirds of the members present at the meeting;

3) Notwithstanding to the provisions of this Proclamation for special voting by the Main Council or the Sub-Council, the members present at the Main Council or the Sub-Council shall pass decision by a majority vote; however, provided, where the Council has given an equal number of votes for and against a decision, the chairperson shall have the casting vote;

4) No member of the Main Council or Sub-Council shall be a member of the Main Council or the Sub-council or a designated committee until a decision has been made on the case of his relatives;

| | |
|---|---|
| በአባልነት አይቀመጥም፤ | |
| 5) በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ጉባዔውም ሆነ ንዑስ ጉባዔዎች እንደአስፈላጊነቱ የራሳቸውን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ውስጠ-ደንብ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ | 5) Without prejudice to the provisions of this Article, both the Main Council and the sub-Council may, as may be necessary, prepare their own internal meeting procedures. |
| **18.<u>ምስጢር ስለመጠበቅ</u>** | **18. Confidentiality** |
| 1) ማንኛውም ጉባዔ በይፋ እንዲገለጹ ያላደረጋቸው የጉባዔ ውይይቶች፣ የቀረቡ ሀሳቦችና የተደረጉ ክርክሮች ይዘት ምስጢራዊነት የተጠበቀ ይሆናል፤ | 1) The content of the meetings, proposals and debates which are not made public by the Councils shall be kept confidential; |
| 2) ማንኛውም የዋና ጉባዔ ወይም ንዑስ ጉባዔ አባል ወይም በጉባዔው ስብሰባዎች የሚሳተፍ ሰው ሚስጢራዊነትን የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ | 2) Any member of the Main Council, Sub-Council, or anyone who attends a meeting shall have a duty of confidentiality. |
| **19.<u> ከጉባዔ አባልነት መሰናበት ወይም መልቀቅ</u>** | **19. Termination or Removal from the Memmbership of Council** |
| 1) የማንኛውም ጉባዔ አባል ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ከጉባዔ አባልነት ሊሰናበት ይችላል፡- | 1) Any member of the Council may be dismissed from the Council for the following grounds:- |
| ሀ) ከደንብ መተላለፍ ውጭ በሆነ ወንጀል ከተፈረደበት፣ | a) where he is convicted for criminal offence except for minor contraventions ; |
| ለ) በግል የጤና ችግር ምክንያት ኃላፊነቱን በአግባቡና በብቃት ማከናወን ከተሳነው፣ | b) Failure to fulfill his functions properly and efficiently due to personal health problem; |
| ሐ) የዚህን አዋጅ ወይም የጉባዔውን የውስጥ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት | c) When a decision is made by a two- |

ባለማክበሩ ምክንያት ከአባልነቱ እንዲሰናበት በጉባዔው አባላት በሁለት-ሦስተኛ ድምጽ ሲወሰንበት፤

2) የማንኛውም ጉባዔ አባል ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች የጉባዔ አባልነቱን ሊተው ይችላል፡-

ሀ) በምርጫ ወይም በሹመት ከነበረበት የሥራ መድብ ሲለቅ፣

ለ) አባል ከሆነበት ጉባዔ የአስተዳደር ወሰን ውጭ በሆነ የስራ ዝውውር ወይም ቀድሞ ከነበረበት የሥራ መደብ ወይም ስፍራ ሲለቅ፣

ሐ) በፍላጎቱ ለመልቀቅ ሲጠይቅ፡፡

3) የማንኛውም ጉባዔ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ለመልቀቅ የወሰነ እንደሆነ ይህንኑ ከአንድ ወር አስቀድሞ ለሚመለከተው የጽሕፈት ቤት ኃላፊ በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት፤

4) ጉባዔው በተሰናበተ ወይም አባልነቱን በተወ አባል ምትክ ተገቢውን ሰው በተቻለ ፍጥነት መተካት አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት
## የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ጽሕፈት ቤቶች አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባር

### ንዑስ ክፍል አንድ
### የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት፣

thirds majority of the members of the Council to remove him for disobeying this Proclamation or the internal procedures of the Council;

2) Any member of the Council may be removed from Council membership for the following grounds:-

a) When resigns from his previous position by election or appointment;

b) When resigns from a position out of the administrative boundary of his constituency or from his previous deployment or position;

c) Where resigns voluntarily.

3) when any member of the Council decides to resign in accordance with sub-article 2 of this article, shall notice the relevant head of the Office in writing one month in advance;

4) The council shall replace in the position of the removed or resigned members as soon as possible.

## Part Three
## Organization, Powers and Functions of the Offices of the Judicial Administration Council

### Subsection One
### Organization, powers and functions of the

| ሥልጣንና ተግባር | Main Council Office |
|---|---|
| 20.የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት | **20. Organization of the Main Council Office** |
| የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡- | Main Council Office shall have the following organization:- |
| 1) የጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፣ የሥራ ክፍሎችና በጀት ይኖረዋል፤ | 1) head of the Office , the necessary staff, departments and budget; |
| 2) የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በዋና ጉባዔው ሰብሳቢ አቅራቢነት በዋና ጉባዔው ይሾማል፤ | 2) Head of the Office shall be appointed by the Main Council up on the recommendation of the chairperson of the Main Council; |
| 3) የጽሕፈት ቤት ኃላፊው ተጠሪነት ለጉባዔው ሰብሳቢ ነው፤ | 3) Head of the Office shall be accountable to the chairperson of the Council; |
| 4) የጽሕፈት ቤት ኃላፊ የጉባዔው ስብሰባዎች ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፤ | 4) Head of the Office shall serve as the secretary of the meetings of the Council; |
| 5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ለየጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔም ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ | 5) Without prejudice to the details mentioned under sub article 1-4 of this article, the office of the main Council shall serve as the office of sub-council, too. |
| 6) የዋናው ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ዝርዝር አደረጃጀት ዋና ጉባዔዉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡ | 6) Details of organization of the Office of the Main Council shall be determined by a directive to be issued by the Main Council. |

| | |
|---|---|
| **21.<u>የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>** | **21. Powers and functions of the Office of the Main Council** |
| የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡- | Main Council Office shall have the following powers and functions:- |
| 1) የጉባዔውን ረቂቅ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና የማስፈጸሚያ በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል፤ | 1) Prepares draft annual work plan and implementation budget of the Council and, when approved, administers the budget; |
| 2) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶችንና ምክትል ፕሬዚደንቶችን እንዲሁም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ የሚሰሩ የዋና ጉባዔ እና የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎችን አስመልክቶ በሚቀርቡ አቤቱታዎች መነሻነት የሥነ-ምግባር ጉድለት መፈጸሙን የሚያሳይ ነገር ካለ ከዋና ጉባዔ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር ምርመራ እንዲካሄድ እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከተው ኮሚቴ ይመራል፣ በአቤቱታዎቹ ላይ ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ንዑስ ጉባዔ ያቀርባል፤ | 2) if it admits that there is evidence of misconduct in the proceedings of the Supreme Court judges, the Presidents and Vice-Presidents of the High Court and appointees of the Main and Sub Council work at the level of the Supreme Court, in consultation with the Chairperson of the Main Council, conduct an investigation on them and, as may be necessary, refer it to the relevant committee; submits recommendation to the Supreme Court Sub-Council; |
| 3) የክልሉ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ ለዚህም ግልጽ የሆነ የቅሬታ አቀራረብና አቀባበል ሥርዓት ይዘረጋል፤ | 3) Receives greivances against the judicial services provided by the regional courts; establish a system for grievance submission; |
| 4) በንዑስ ጉባዔው የተሰጠ የውሳኔ ሀሳብ | 4) Upon submission of the recommendations of the sub-Council to the Main Council |

| | |
|---|---|
| ለዋና ጉባዔ ሲቀርብ እንዲሁም በንዑስ ጉባዔ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ የቀረበ እንደሆነ ዝርዝር ሁኔታው እንዲመረመርና እንዲጣራ ካደረገ በኋላ የበኩሉን አስተያየት አዘጋጅቶ ለዋና ጉባዔው ያቀርባል፤ | and, after considering the details of the appeal of the sub-Council's decision, prepares and submits its own opinion to the Main Council; |
| 5) ዋና ጉባዔው የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በጉባዔው ሰብሳቢ ፊርማ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሰዎችና አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ | 5) The decisions given by the Main Council shall be signed by the Chairperson of the Council and shall be delivered to the relevant parties in time; follows up its implementation; |
| 6) የዳኝነት ዘርፉን የሰው ኃይል ልማትና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች በመዘርጋት በክልሉ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ወጥነት ያለው የፍትሕ ሥርዓት እንዲሰፍን ይሰራል፤ | 6) Works by setting the human resources and capacity building programs of the judiciary to ensure a consistent justice system in the regional courts; |
| 7) በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የፍርድ ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ጥናት ያካሂዳል፣ በመዛግብት ላይ ምርመራ ያደርጋል፣ ግብረ መልስ ለዋና ጉባዔ ያቀርባል፤ | 7) Establish a system to ensure the quality of justice in the courts at all levels, conduct research, investigate cases, and provides feedback to the Main Council; |
| 8) ለሥነ-ምግባር ጉድለት መንስዔ ይሆናሉ ተብለው የሚታመንባቸውን ጉዳዮች በየጊዜው እያጠና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለዋና ጉባዔው ያቀርባል፤ | 8) Regularly study the issues that are believed to be the cause of the misconduct and make recommendations to the Main Council; |
| 9) የክልሉን ፍርድ ቤቶች አጠቃላይ | 9) Performs periodic surveys of the overall judicial performance of the regional courts, organizes and proposes |

| | |
|---|---|
| የዳኝነት ሥራ አፈፃፀም በተመለከተ በየጊዜው የዳሰሳ ጥናት ያካሄዳል፣ የማሻሻያ ሃሳቦችን እያደራጀ ለዋና ጉባዔውያቀርባል፤ | amendments to the Main Council; |
| 10) የክልሉን ዳኞችና የጉባዔ ተሿሚዎች የሥራ አፈጻጸም ምዘና ተግባራዊነትን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ወቅታዊ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለጉባዔው ያቀርባል፣ የግል ማህደር ያደራጃል፣ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቶችና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በማህደሮች ውስጥ መግባታቸውን ያረጋግጣል፤ | 10) Follows up the implementation of the performance appraisal of the judges and appointees of the region; prepares regular reports and submits it to the Council, organizes personal archives; ensures that the performance appraisal results and other relevant information are entered in the archives; |
| 11) በጽሕፈት ቤቱ ሥር ያለ የጉባዔ ተሿሚዎችንና የሥራ ኃላፊዎችን የሥራ አፈጻጸም ምዘና ያካሄዳል፤ | 11) Conduct an evaluation of the performance of Council appointees and heads under the Office ; |
| 12) የክልሉን ዳኞች አስተዳደራዊ ጉዳዮች አፈጻጸም ይከታተላል፤ | 12) Follows-up the administrative affairs of the judges of the region; |
| 13) የዋና ጉባዔን የስብሰባ ቃለ-ጉባዔዎችና ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፤ | 13) Maintains and holds the minutes and other documents of the Main Council; |
| 14) ለንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ | 14) Provides necessary support to the sub-Council Offices; |
| 15) እንደ አግባቡ በዋና ጉባዔና በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡ | 15) Perform such other functions as may be provided by the Main Council and the chairperson. |
| 22.<u>የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u> | **22. Powers and Functions of the Head of the Main Council Office** |

| | |
|---|---|
| የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነት ለዋና ጉባዔው ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦ | Head of the Office shall be accountable to the chairperson of the main Council and shall have the following powers and functions:- |
| 1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ድንጋጌ መሠረት ለጽሕፈት ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ስራ ላይ ያውላል፤ | 1) Exercise the powers and functions assigned to the Office in accordance with the provisions of Article 21 of this Proclamation; |
| 2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጽሕፈት ቤት ኃላፊው የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦ | 2) Notwithstanding to the main provisions of sub-article (1), head of the Office shall have the following powers and functions:- |
| ሀ) ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው ጉባዔውን በፀሐፊነት ያገለግላል፣ | a) serve as the secretary of the Council without a vote; |
| ለ) የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፣ ቃለ-ጉባዔዎችና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች በጉባዔው አባላት መፈረማቸውንና በጥንቃቄ መያዛቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ | b) Holds the minutes of the Council; follows-up and verifies that the minutes and other related documents are signed and maintained by the members of the Council; |
| ሐ) ከጉባዔው ሰብሳቢ ጋር በመነጋገር የጉባዔውን አጀንዳዎች ያደራጃል፣ ከጉባዔው ስብሰባ ቀን አስቀድሞ አጀንዳዎቹን ለአባላት ያሰራጫል፣ መድረሳቸውንም ይከታተላል፣ | c) In consultation with the chairperson of the Council, organize the agendas of the Council; disseminates the agendas to the members before the meeting; follows-up their arrival; |
| መ) የጽሕፈት ቤቱንና በሥሩ ያሉ የሥራ ክፍሎችን የዕለት-ተዕለት ሥራዎች በኃላፊነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣ | d) Directs, coordinates, and supervises the day-to-day functions of the departments; |
| ሠ) የጉባዔው የተለያዩ ኮሚቴዎች ቢሮ በማደራጀት የኮሚቴዎቹን | e) Organize office for the various |

ባለሙያዎችና ረዳት ሠራተኞችን ይመድባል፣

ረ) የጉባዔውን ረቂቅ ዓመታዊ የሥራ እቅድ እና የማስፈጸሚያ በጀት አዘጋጅቶ ለጉባዔው ሰብሳቢ ያቀርባል፣

ሰ) የጉባዔውን የስራ እቅድና አፈጻጸም አስመልክቶ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣

ሸ) የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

ቀ) በጉባዔውና በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር**

**23. የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት**

የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት አደረጃጀት ይኖሩታል፡-

1) የጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፣ የሥራ ክፍሎችና በጀት ይኖረዋል፤
2) የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በንዑስ ጉባዔው ሰብሳቢ አቅራቢነት በንዑስ ጉባዔው ይሾማል፤
3) የጽሕፈት ቤት ኃላፊው ተጠሪነት

committees of the council and assign the experts and assistants of the committees;

f) Prepare draft annual work plan and implementation budget of the Council and submit it to the chairperson of the Council;
g) Provides up-to-date reports on the work plan and implementation of the Council;
h) Administers and supervises the staff of the Office;
i) Performs such other functions as may be provided by the Council and the chairperson.

**Subsection Two**

**Organization, powers and functions of the sub-council Office**

**23. Organization of the Sub-Council Office**

Sub-Council Office shall have the following organization:-

1) head of the Office, necessary staffs, departments and budget;
2) head of the Office shall be appointed by the sub-Council up on the approval of the chairperson of the sub-Council;
3) head of the Office shall be accountable to the chairperson of the sub-Council;

ለንዑስ ጉባዔው ሰብሳቢ ነው፤

4) የጽሕፈት ቤት ኃላፊ የንዑስ ጉባዔው ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፤
5) የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ዝርዝር አደረጃጀት ዋና ጉባዔዉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

24.<u>የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

1) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞችን፣ የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችንና ዳኞችን እንዲሁም በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ የሚሰሩ የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎችን በተመለከተ የሥነ-ምግባር ጉድለት መፈጸሙን የሚያሳይ ነገር ካለ እንደሆነ ከንዑስ ጉባዔው ሰብሳቢ ጋር በመመካከር ምርመራ እንዲካሄድና እንደአስፈላጊነቱ የዲሲፕሊን ክስ እንዲመሠረት ያደርጋል፤
2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 ለዋና ጉባዔው ጽሕፈት ቤት በዝርዝር የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት አግባብነታቸው እየታየ ለንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤትም በተመሳሳይ ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

25.<u>የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የንዑስ ጉባዔው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተጠሪነት

4) head of the Office shall serve as the secretary of the sub-council;
5) Details of the sub-council Office shall be determined by a directive to be issued by the Main Council.

**24. Powers and functions of the Office of the Sub-Council**

1) In consultation with the Chairperson of the Sub-Council, if there is an evidence of misconduct in the case of high court judges, wereda court presidents and judges, as well as sub-council appointees at the high court level, conduct an investigation and, as may be necessary, effect disciplinary proceedings;
2) The powers and functions given in detail to the Office of the Main Council in Article 22 of this Proclamation shall also be applicable to the sub-council up on relevance.

**25. Powers and Functions of the Head of the Sub-Council office**

Head of the sub-council office shall be accountable to the chairperson of the sub-

ለንዑስ ጉባዔው ሰብሳቢ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሠረት ለዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደአግባብነቱ ለንዑስ ጉባዔው ጽሕፈት ቤት ኀላፊ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት
## የዳኞችና የጉባዔ ተሿሚዎች ምልመላ፣ ሹመት፣ የደረጃ ዕድገት፣ ዝውውርና ስንብት

26.የዳኛ ሆኖ ለመሾም የሚያበቁ መመዘኛዎች

1) የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በክልሉ ፍርድ ቤቶች ዳኛ ሆኖ መሾም ይችላል፡-

ሀ) በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

ለ) በሕግ ትምህርት ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው፣

ሐ) መልካም ስነ-ምግባር ያለውና ከማንኛውም ሱስና ያልተገባ ልማድ ነጻ የሆነ፣

መ) የዳኝነት ሙያ የሚጠይቀውን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመሸከም የሚያስችል ዕውቀትና ክህሎት የተላበሰ፣ ሥራ ወዳድ፣ ታታሪ፣ ቅን፣ ሀቀኛና ታማኝ የሆነ፣

ሠ) ለሕግ የበላይነት መከበርና ለፍትሀዊ አሰራር ቁርጠኛ የሆነ፣

ረ) ዳኛ ሆኖ ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ፣

ሰ) ከደንብ መተላለፍ ውጭ በወንጀል ተከሰ

Council, and powers and functions assigned to the head of office in accordance with Article 23 of this proclamation shall apply to the head of sub-council office as may be appropriate.

## Part Four
## Recruitment, appointment, promotion, transfer and termination of tenure of judges and appointees of the Council

**26. Qualifications for appointment as a judge**

1) Any person who meets the following requirements may be appointed as a judge of the Regional Courts:-

a) Be an Ethiopian National;

b) Holds at least LLB degree in law;

c) Have Good ethics and be free from morally unacceptable conduct;

d) Knowledgeable, skilled, hardworking, probity, integrity, honesty to carry out the highest responsibilities required by the judiciary.

e) Have a sense of justice and is committed to respect for the rule of law;

f) Be Willing to serve as a judge;

g) Be free from criminal conviction except for minor contraventions;

h) Be not less than 25 years old for the

ያልተቀጣ፣

ሸ) ዕድሜው ለወረዳና ለከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከ25 ዓመት፣ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ከ28 ዓመትና ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ ከ30 ዓመት ያላነሰ፤

2) የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ዕጩ ዳኞችን ለመመልመል የሚያገለግል ተጨማሪ መስፈርት ሊዘጋጅ ይችላል፣ ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

27.<u>የጉባዔ ተሿሚ ሆኖ ለመቅረብ የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

1) አጠቃላይ የክልሉን ፍርድ ቤቶች ዓላማ ማሳካት እንደሚችል የታመነበት ማንኛውም ሰው ለጉባዔዎች ተሿሚነት እጩ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው አጠቃላይ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ የዋና ጉባዔም ሆነ የንዑስ ጉባዔ ተሿሚ ሆኖ ለመቅረብ የሚያበቃ የስራውን ልዩ ጠባይና ውስብስብነት ከግምት ያስገባ መስፈርት ይዘጋጃል፤ ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

28.<u>የዕጩ ዳኞች ሹመት</u>

1) በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚሰሩ ዕጩ ዳኞች በክልሉ ዋና ጉባዔ

Woreda and City Administration First Instance Court, 28 years for the High Court and 30 years for the Supreme Court;

2) Additional criteria may be set for the recruitment of judges based on the status of the Region; details shall be determined by a directive to be issued by the Supreme Court.

**27. Requirements to be a Candid for Council Appointee**

1) Any person who is believed to be able to achieve the objectives of the Region Courts may be appointed as a candidate for the Council;

2) Notwithstanding to the main principle set out in sub-article 1), a requirement shall be prepared taking into account the special nature and complexity of the work, which results in the nomination of both the Main Council and Sub-Council; details shall be determined by directive to be issued by the Supreme Court.

**28. Appointment of Candid Judges**

1) The judges of the courts at all levels shall be appointed by the State Council up on the recommendation of the Main Judicial

አቅራቢነት በክልል ምክር ቤት ይሾማሉ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሹመቱ በክልል ምክር ቤት ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት፣ የክልሉ ዋና ጉባዔ፡-

ሀ) የከፍተኛና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመትን አስመልክቶ የፌዴራል ፍርድ ቤት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔን አስተያየት መጠየቅ እና ይህንኑ ማካተት አለበት፣ሆኖም በሦስት ወር ጊዜ አስተያየት ካለቀረበ የዕጩ ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

ለ) ለወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ሲሆን ደግሞ የሚመለከተውን የዞን አስተዳደር ምክር ቤት አስተያየት መጠየቅ እና ይህንኑ ማካተት አለበት፡፡

## 29.<u>የደረጃ ዕድገትና ዝውውር</u>

1) የዳኞችና የጉባዔ ተሿሚዎች የደረጃ ዕድገት የሚወሰነው በክልል ዋና ጉባዔ ነው፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፤

2) የዳኞችና የጉባዔ ተሿሚዎች ከአንድ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ በተመሳሳይ እርከን ላይ ወደ ሚገኝ ፍርድ ቤት ወይም ከአንድ ምድብ ችሎት ወደ ሌላ ምድብ ችሎት የሚደረግ የስራ ቦታ ዝውውር የሚፈጸመው እንደ

Council;

2) Notwithstanding to the provisions of sub-article (1) of this article, prior to the appointment is submitted to the State Council for approval, the Main Judicial Council shall:-

a) Request the opinion of the Federal Judicial Adminstration Council on the appointment of the High and Supreme Court judges and shall include this; however, if no opinion is submitted within three months, the appointment of candidate judges shall be submitted to the State Council.

b) When an appointment is for the Wereda Court Judges, request for opinion of the relevant zonal Administration Council and include the opinion thereof;

## 29. Promotion and Transfer

1) The promotion of judges and appointees of the council shall be determined by the Main Council; details shall be determined by directive;

2) The transfer of judges and appointees of the council from one court to another in a court of the same level or from one division bench to another division bench shall be carried out in accordance with the decision of the Main Council or sub-

አግባብነቱ በክልል ዋና ጉባዔ ወይም በንዑስ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ይሆናል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፤

3) አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜና በቂ ምክንያት ሲኖር ዋና ጉባዔው የዳኛውን ፈቃደኝነት በመጠየቅ ከአንድ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ፍርድ ቤት መድቦ ሊያሰራ ይችላል፡፡

**30.ደመወዝ፣ አበልና ጥቅማጥቅም**

1) የዳኞች፤ የጉባዔ ተሿሚዎች፤ ፕሬዚደንቶች እና ምክትል ፕሬዚደንቶች ደመወዝ፣ አበልና ጥቅማጥቅም የሚወሰነው በክልል ዋና ጉባዔ ነው፤

2) አግባብነት ያላቸው የዳኞችን መብቶችና ጥቅሞች የሚደነግጉ ህጎች እንደተጠበቁ ሆነው በስራ ላይ ያለ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ ም/ፕሬዝዳንት፣ ዳኞች፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንትና ም/ፕሬዝዳንት የቪ.አይ.ፒ/ VIP/ አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

3) የክልል ዋና ጉባዔ በንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት ደመወዝ፣ አበልና ጥቅማጥቅም ሲወስን የዳኝነት ሙያ የሚገባውን ክብር፣ የሥራውን ክብደትና ጫና፣ ኃላፊነቱ በዳኞች፣ በተሿሚዎችና በፕሬዚደንቶች ላይ የሚጥለውን ገደብ፣ የኑሮ ሁኔታና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች

council as may be appropriate; details shall be determined by directive;

3) When it is deemed necessary and reasoned, the Main Council may, with the consent of the judge, transfer him from one court to another.

**30. Salary, Allowances and Benefits**

1) The salaries, allowances and benefits of judges and appointtes of the council, and the salaries and benefits of presidents and vice-presidents shall be determined by the Main Judicial Council;
2) Without prejudice to the relevant laws governing the rights and benefits of judges, the President, Deputy President, Judges, High Court President, and Deputy President of the Supreme Court shall have VIP service.

3) In determining salaries, allowances and benefits in accordance with the provisions of sub-article (1), the Main Judicial Council shall take into account the honor of the judiciary, the harshness and burden of its work, the restrictions imposed on judges, appointees and presidents, living

| | |
|---|---|
| ታሳቢ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፤ ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡ | standard and other relevant factors; details shall be determined by directive to be issued by the Supreme Court. |
| 31.<u>የዳኞች ከሥራ መሠናበት</u> | **31. Termination Tenure of Judges** |
| 1) በክልሉ ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ተመድቦ የሚሠራ ዳኛ ከዳኝነት ሥራው ሊሰናበት የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ይሆናል፦ | 1) A judge appointed at any level in the Region may be removed from discharging his duty only for the following grounds: |
| ሀ) በዳኞችና የጉባዔ ተሿሚዎች የሥነ-ምግባርና ዲሲፕሊን ደንብ መሠረት ዳኛው ጥፋት ፈጽሞ በመገኘቱ ወይም ዳኛው ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ በማሳየቱ ወይም በህመም ምክንያት የዳኝነት ሥራውን ማከናወን ባለመቻል ምክንያት ጉባዔው ከዳኝነት ሥራው እንዲሰናበት ሲወስንና ይኸው ውሳኔ በክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ፣ ወይም | a) In accordance with the Code of Conduct and Discipline of Judges and Appointments, the judge shall be removed from his tenure for any misconduct, or manifest incompetence a judge's inability to perform his functions due to illness or for failing to perform his judicial functions due to illness when it is submitted to the State Council and approved by it; or |
| ለ) በሕግ የተደነገገው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሲደርስ፣ ወይም | b) when the statutory retirement age has reached; or |
| ሐ) ዳኛው ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈልግና ይህንኑ ለዋና ጉባዔ ሰብሳቢ በጽሁፍ ገልጾ የሁለት ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ፣ ወይም | c) When the judge wants to resign, and gives two months default notice in writing to the chairperson of the Main Council; or |
| መ) ዳኛው ለሌላ መንግስታዊ የሥራ ኃላፊነት ሲሾምና ሹመቱን ከተቀበለ፤ | d) When the judge is appointed and accepts another public functions; |

| | |
|---|---|
| 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) መሠረት የሥራ መልቀቂያ የሚያቀርበው ፕሬዚዳንቱ ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ሲሆን ሥራውን ከመልቀቁ አስቀድሞ የሦስት ወር ማስጠንቀቂያውን እንደአግባብነቱ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ወይም ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ መስጠት አለበት፣ ሆኖም የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት የዳኝነት ሥራውን ጭምር ለመልቀቅ የፈለገ እንደሆነ ማስጠንቀቂያውን ለክልሉ ዋና ጉባዔ ማቅረብ ይኖርበታል፤ | 2) President or Vice-President shall submit his resignation in accordance with sub-article (1) (c) of this article and shall give three months' default notice to the Chief Executive of the Region or Zonal Chief Administrator as may be appropriate, provided, however, to the Supreme Court, High Court, and Wereda Court president or vice president also intends to resign from work, the default notice shall be submitted to the Main Judicial Council; |
| 3) በንዑስ አንቀጽ (1 (ሐ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የዳኛው ሥራን መልቀቅ በዳኝነት አገልግሎቱ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድርና በሌሎች አማራጮች መሸፈን የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የጉባዔው ሰብሳቢ የዳኛው የሚለቅበትን ጊዜ ከ3 ወር ለማይበልጥ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፤ | 3) When removal of a judge within the period specified in sub-article (1 (c) puts a great strain on the judicial service and cannot be covered by other options, the presiding judge may extend the removal of the judge for a period not exceeding 3 months; |
| 4) በንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት የጉባዔው ሰብሳቢ ጊዜውን ለማራዘም ከወሰነ ይህንኑ ውሳኔ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት ለዳኛው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ካለፈ በኋላ በጉባዔ ሰብሳቢ የሚሰጥ የጊዜ ማራዘሚያ ውሳኔ በዳኛው ላይ አስገዳጅነት አይኖረውም፤ | 4) When chairperson of the Main Council decides to extend the term in accordance with sub-article 3, he shall notify the judge in writing before the period of limitation of the default notice; decision of the Main Council to extend the default notice after its expiration shall not be binding on the judge; |

| | |
|---|---|
| 5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1(ሐ) የተደነገገው ቢኖርም የጉባዔው ሰብሳቢ የተለየ ሁኔታ መኖሩን በተረዳ ጊዜ የሦስት ወር ጊዜን ሳይጠብቅ ለዳኛው መልቀቅያ እንዲሰጠው ሊወሰን ይችላል፤ | 5) Notwithstanding the provisions of sub-article (1) (c) of this article, the Chairperson of the Council may, upon realizing that there is a special situation, grant a resignation to the judge within three months; |
| 6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) ላይ የተመለከተው ውሳኔ የጉባዔ ተሿሚዎች የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ተፈፃሚነት የሚኖረው ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ ነው፡፡ | 6) The decision referred in sub-article (1) (a) of this article, except to the appointees of the Council, shall be applicable after it has been submitted and approved by the State Council. |
| **32. <u>ከሥራ ስለተሰናበተ ዳኛ ክልከላዎች</u>** | **32. Prohibitions of Judge whose tenure is Terminated** |
| 1) ስለጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥ የሚደነግጉ ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ከሥራው የተሰናበተ ዳኛ አስቀድሞ ይሰራበት በነበረ ፍርድ ቤት ያየውን ጉዳይ ማናቸውም ችሎት ፊት በጠበቃነት ተከራካሪዎችን ወክሎ መቅረብ አይችልም፤ | 1) Without prejudice to other laws regarding licensing of attorneys, a judge whose tenure is terminated shall not appear before any bench in which he served as a judge representing litigants; |
| 2) ማንኛውም ሥራ የለቀቀ ዳኛ በጥብቅና ሥራ በመሰማራቱ ለዳኞች አግባብ ባለው ሕግ የተፈቀዱ ጥቅማጥቅሞችን ከማግኘት አያግደውም፤ | 2) Any judge in the attorney service shall not lose benefits permitted under other relevant laws prior to his resignation; |
| 3) በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራው የተሰናበተ ዳኛ ከሥራ ስንብት ጋር በተያያዘ ለዳኞች በሕግ የተፈቀዱ ከጡረታ ውጭ ያሉ ጥቅማጥቅሞችን አያገኝም፡፡ | 3) A judge whose tenure is terminated on grounds of breach of discipline shall not be entitled to receive benefits other than pension payable by law upon termination of tenure of judges. |

| | |
|---|---|
| 33.<u>የጉባዔ ተሿሚዎች ከሥራ መሰናበት</u> | **33. Termination of Tenure of the Council Appointees** |
| ማንኛውም የጉባዔ ተሿሚ ከሥራ ሊሰናበት የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡- | Any appointee of the Council may be terminated from his tenure for the following grounds:- |
| 1) በሕግ የተደነገገው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሲደርስ፤ | 1) When attains retirement age provided by law; |
| 2) የጉባዔ ተሿሚው ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ከለቀቀ፤ | 2) When voluntarily resigns his appointment of the Council; |
| 3) በዳኞችና በጉባዔ ተሿሚዎች የሥነ-ምግባርና ዲሲፕሊን ደንብ እንደተደነገገው የጉባዔ ተሿሚው ጥፋት ፈጽሞ በመገኘቱ፣ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ በማሳየቱ ወይም በህመም ምክንያት ሥራውን ማከናወን ባለመቻሉ ምክንያት አግባብነት ያለው ጉባዔ ከሥራው እንዲሰናበት ሲወስን፤ | 3) When the appropriate council decides to terminate the appointee where committed a breach of discipline, manifest incompetence, or inability to perform his functions due to illness, and ascertained by the Judicial Administration Council and a decision is made to remove; |
| 4) በወንጀል ተከሶ ጥፋተኝነቱ ከተረጋገጠና በጥፋቱ ከባድነት ምክንያት ለሥራው ብቁ ሆኖ ያልተገኘ ከሆነ፤ | 4) Where convicted of a crime and manifest incompetence for the job due to the seriousness of the offense; |
| 5) የጉባዔ ተሿሚው ለሌላ መንግሥታዊ የሥራ ኃላፊነት ሲሾምና ሹመቱን ከተቀበለ፤ | 5) Where the council appointee accepts and appointed for another public duty; |
| 34. <u>በሥነ-ምግባር ጥሰት ምክንያት ክስ ስለማቅረብ</u> | **34. Complaint on Judicial Misconduct** |
| 1) በዳኝነት ሥራ አካሄድ ላይ ግልጽ የሆነ የዳኝነት ሥነ-ምግባር ጥሰት ተፈጽሟል | 1) Any person who is of the belief that a judge acted in violation of the judicial |

ብሎ ያመነ ወይም ስለመፈጸሙ አንዳች ማስረጃ ያለው ማንኛውም ሰው ለጉባዔ ወይም ለንዑስ ጉባዔ አቤቱታ ወይም ጥቆማ ማቅረብ ይችላል፤

2) የሥነ-ምግባር ጥሰት ተፈጽሟል በሚል ምክንያት በዳኛ ወይም በጉባዔ ተሿሚ ላይ የዲስፕሊን ክስ የቀረበ እንደሆነ ክሱ በአጭር ጊዜ ታይቶ ውሳኔ ማግኘት አለበት፡፡ በሂደቱም ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ የማወቅ እና የመከላከል መብት ይጠበቅለታል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

3) የሥነ-ምግባር ጥፋት ፈጽሞ በተገኘ ዳኛ ወይም የጉባዔ ተሿሚ ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ በሕገ-መንግሥት፣ በዚህ አዋጅ እና በሥነ-ምግባር እና ዲስፕሊን ደንብ ውስጥ የሰፈሩትን ድንጋጌዎች የተከተለ መሆን ይኖርበታል፤

4) የሥነ-ምግባር ጥሰት አቤቱታ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የማወቅ መብት አለው፤

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ለዳኞች የተጠበቁ መብቶችና በዳኞች ላይ የተጣሉ ገደቦች</u>

### 35. <u>የመደራጀት መብት</u>

1) ዳኞች የዳኝነትን ሥርዓት የማጎልበት፣ የአባላቱን ነፃነትም ሆነ ሙያዊ ሥነ-

Code of Conduct or any one with evidence on such violation may submit a petition, complaint or provide information to the Council or sub council;

2) Where there is a disciplinary charge against a judge or a court appointee for misconduct, the case shall be reviewed and a decision shall be made as soon as possible. In the process, the defendant is entitled to know and defend the charges against him. Details shall be determined by the Regulation;

3) Disciplinary action against a convicted judge or appointee of the Council shall be in accordance with the provisions of the Constitution, this Proclamation and the Code of Conduct and Discipline;

4) Any person who files a complaint of misconduct has the right to know the decision on the case;

## **Part Five**

## **Rights Reserved for Judges and Restrictions Imposed on Judges**

### **35. The Right to Organize**

1) Judges may establish an association with the aim of enhancing the judicial system,

ምግባር የማስከበርና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ዓላማ ያለው ማኅበር ሊያቋቁሙ ይችላሉ፤

2) ማንኛውም ዳኛ የዳኞች ማኅበር አባል ለመሆን መብት አለው፡፡

**36. ያለመከሰስ መብት**

1) ዳኞች በሰጡት ወይም በሚሰጡት ውሳኔ ምክንያት በፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብባቸው አይችልም፤

2) ማንኛውም ዳኛ ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፈንጅ ካልተያዘ ወይም በጉባዔ ያለመከሰስ መብቱ ካልተነሳ በስተቀር አይያዝም፣ አይታሰርም ወይም ክስ አይቀርብበትም፤

3) የዳኞች ያለመከሰስ መብት የሚነሳበት ሥነ-ሥርዓት በዳኞች የዲሲፕሊን ደንብ በተደነገገው አግባብ ይሆናል፡፡

**37. ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት**

የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነት መርሆዎችን ወይም የዳኞች የሥነ-ምግባርና ዲሲፕሊን ደንብ ድንጋጌዎችን የሚቃረን ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ማንኛውም ዳኛ በሕገ- መንግሥት እና በሌሎች ሕጎች ለዜጎች የተረጋገጠ የመናገር፣ የመጻፍ ወይም በማንኛውም መንገድ ሀሳብን መግለጽ ነጻነት አለው፡፡

**38. በማኅበራዊ እና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች የመሳተፍ መብት**

የዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነት መርሆዎችን ወይም

ensuring the independence and professional ethics of its members, and ensuring accountability;

2) Every judge has the right to be a member of the Judges' Association.

**36. Judicial Immunity**

1) Judges may not have civil liability for actions taken in their official capacity;

2) A judge may not be arrested, detained or prosecuted unless caught flagrante delicto in grave crimes or his immunity is lifted by the main judicial council;

3) The detail procedure of lifting of judges 'immunity shall be in accordance with the provision of the regulation of the judges disciplinary code.

**37. Freedom of Expression**

A Judge shall have the right to speak, write, participate in social and religious affairs, participate in training and research undertakings as provided for and guaranteed under the Constitution and other laws provided this may not be inconsistent with the principles of judicial independence and impartiality.

**38. The right to participate in social and religious affairs**

Any judge has the right to participate in

| | |
|---|---|
| የዳኞች የሥነ-ምግባርና ዲሲፕሊን ደንብ ድንጋጌዎችን የሚቃረን ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ማንኛውም ዳኛ በማኅበራዊና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች የመሳተፍ መብት አለው፡፡ | social and religious affairs, provided this may not be inconsistent with the principles of judicial independence and impartiality or the Code of Conduct and Discipline of Judges. |
| 39.<u>የዳኛ እረፍት</u> | **39. Leave of a Judge** |
| 1) ማንኛውም ዳኛ ከነሐሴ 1 ቀን እስከ መስከረም 30 ቀን መደበኛ የሆነ የዓመት እረፍት ይኖረዋል፤ | 1) Any judge shall have a regular annual leave from Hamle 1 to Meskerem 30 by Ethiopian calendar; |
| 2) በንዑስ አንቀጽ 1) የተደነገገው ቢኖርም ዳኛው ልዩ ሁኔታ ወይም አስገዳጅ ምክንያት ባጋጠመው ጊዜ ከሚመለከተው የፍርድ ቤት ሀላፊ ጋር ተነጋግሮ ከመደበኛ የዓመት እረፍት ተቀናሽ የሚደረግ የተወሰነ ጊዜ ሊጠቀም ይችላል፤ | 2) Notwithstanding the provisions of sub-article (1), the judge may, in the event of special circumstances or compelling reasons, consult with the President of the relevant court and may use a limited period to be deducted from regular annual leave; |
| 3) በንዑስ አንቀጽ 1) እና 2) በተጠቀሰው ምክንያት የዳኝነት አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ በደረጃው የሚገኝ የፍርድ ቤት ፕሬዚደንት የትኛውንም የፍርድ ቤቱ ዳኛ በተረኛ ችሎት ላይ መድቦ ሊያሠራ ይችላል፤ | 3) Subject to sub-articles 1) and 2) of this article in order to prevent the termination of the judicial service, the President of the court may appoint any Judge of the Court to serve on duty; |
| 4) በእረፍት ጊዜው ለሚሰራ ዳኛ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ ይከፈለዋል፤ | 4) Overtime payment is made to a judge who works during his leave; |
| 5) ባልተቋረጠ ሁኔታ ከአስር ዓመት ያላነሰ ጊዜ ያገለገለ ማንኛውም ዳኛ ዋና ጉባዔው በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ጥናትና ምርምር ለማድረግ እስከ ስድስት ወር የሚደርስ ደመወዝ የሚከፈልበት ልዩ | 5) A judge who has completed uninterrupted service of at least 10 years shall have the right to up to 6 months research leave necessary for research undertakings; |

ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፤

6) ከወሊድ ጋር በተያያዘ ሴት ዳኛ የአራት ወራት የወሊድ ፈቃድ፣ ወንድ የአሥር የሥራ ቀናት የአባትነት ፈቃድ ይኖራቸዋል፤

7) ከንዑስ አንቀጽ 5) በስተቀር የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ለጉባዔ ተሿሚዎችም በተመሳሳይ ተፈጻሚነት አላቸው፤

8) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎችና ሌሎች የፈቃድ ዓይነቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ዝርዝር ሁኔታና አፈጻጸም ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

40.<u>የዳኞች የአገልግሎት ዘመን</u>

1) የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜ 65 ዓመት ሆኖ ዳኛው በ60 ዓመት ጡረታ ሊወጣ ይችላል፤
2) ማንኛውም በዳኝነት እና በሌላ መንግሥት ሥራ 20 ዓመት ያገለገለ ዳኛ ከአቅም በላይ በሆነ የህመም ምክንያት የዳኝነት ሥራውን ማከናወን ያልቻለ እንደሆነ ዋና ጉባዔው ጡረታ እንዲወጣ ሊወስን ይችላል።
3) ማንኛውም 25 (ሃያ አምስት) ዓመት በመንግስት ሥራ ያገለገለ ዳኛ ከ55 (ሃምሳ አምስት) ዓመት እድሜው ጀምሮ ጡረታ ሊወጣ ይችላል፤

6) A female judge is entitled to four months maternity leave while a male judge is entitled to a ten working days of paternity leave;

7) Except sub-article 5, this article shall apply equally to the appointees of the Council;

8) Detail conditions of this Article and other types of leaves shall be determined by a directive to be issued by the Supreme Court.

**40. Tenure of Judges**

1) Mandatory age of retirement of any judge is 65 years; a judge may retire at the age of 60 years if he wishes to do so.
2) Any judge who works as a judge and in public service for 20 years may retire at the age and unable to perform his functions due to incapacity, the Main Council may decide to retire.
3) Any judge who has served in the public service for 25 (twenty five) years may retire at the age of 55 (fifty five);

4) ከጡረታ ጋር ተያያዥነት ባላቸውና በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ሌሎች ጉዳዮች የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው ህግጋት በዳኞች ላይ በተመሳሳይ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

41. <u>የፖለቲካ ድርጅት አባል ወይም ደጋፊ መሆን ስለመከልከሉ</u>

1) የዳኞች የፖለቲካ እንቅስቃሴ አራማጅነት፣ አባልነት፣ ደጋፊነት ወይም በፖለቲካ ድርጅት ስብሰባዎች መሳተፍ የተከለከለ ነው፤

2) ማንኛውም ዳኛ በግልም ሆነ የፖለቲካ ድርጅትን ወክሎ በምርጫ ለመወዳደር የፈለገ እንደሆነ ምርጫው ከሚካሄድበት ቀን አንድ ዓመት አስቀድሞ የዳኝነት ሥራውን መልቀቅ አለበት፤

3) በንዑስ አንቀጽ (1) የተጣለው ገደብ የዳኛውን የመምረጥ መብት አይመለከትም፡፡

<u>**ክፍል ስድስት**</u>

<u>**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**</u>

42. <u>**ቃለ-መሀላ**</u>

ማንኛውም ዳኛ ተሹሞ ስራ ከመጀመሩ በፊት በክልሉ ምክር ቤት ፊት በአካል ቀርቦ የሚከተለውን ቃለ-መሀላ ይፈጽማል፡፡ ‹‹ እኔ ----------- በዛሬው ዕለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጠቅላይ/ የከፍተኛ/ የወረዳ/የመጀመሪያ ደረጃ

4) The relevant laws applicable to civil servants in matters relating to retirement and other matters not covered by this Proclamation shall apply equally on judges and appointees of the council.

**41. Prohibition against Membership in a Political Party and Political Participation**

1) The political activism, membership, support or participation of judges in political parties is prohibited;

2) Any judge who wishes to run for political office may do so provided he resigned judicial post at least one year in advance of the Election;

3) The prohibition provided for in sub-article (1) shall not apply to the right of a judge to elect.

**Part Six**

**Miscellaneous Provisions**

**42. Oath**

Any judge appointed at any level shall before assuming responsibilities take oath infront of the State council being in person "I ------- today as a South Ethiopia Region

| | |
|---|---|
| ፍ/ቤት ዳኛ ሆኜ ተሹሜ ስራዬን ስጀምር ከህዝብና መንስግስት የተጣለብኝን ከፍተኛ ሀላፊነት በታማኝነትና በትጋት ለመወጣት፤ ህገ መንግስቱን እና ህግን ብቻ መሰረት በማድረግ ስራዬን ለመፈፀም ቃል እገባለሁ፡፡›› | Suprme/ High/ Wereda/ First Instance court judge do swear that I will administer justice and protect rule of law with absolute impartiality, independence and diligence only based on the constitution and laws." |
| **43.<u>የዋና ጉባዔ ውሳኔ ተፈፃሚነት</u>** | **43. Applicability of the Main Council Decision** |
| የክልሉ ዋና ጉባዔ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚሰጠውን ውሳኔ ማንኛውም ግለሰብ ድርጅት የመንግስት አካልና ባለስልጣን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ | Any individual, organization, government body, and official have the duty to respect the decision of the Main Council of the Region according to the power given by law. |
| **44.<u>መሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>** | **44. Transitional provision** |
| 1. ይህ አዋጅ ከመፅደቁ በፊት ተሹመው በስራ ላይ የሚገኙ ዳኞች፣ ረዳት ዳኞች፣ ሬጅስትራሮች እና በጉባዔ የሚተዳደሩ ባለሙያዎች ለተሾሙበትና በመስራት ላይ ለሚገኙበት ፍርድ ቤት በክልሉ ህገመንግስት እንደተሾሙ ተቆጥረው ስራቸውን ይቀጥላሉ፡፡ | 1. Judges, assistant judges, registrars, and experts administered by the council and working before the approval of this proclamation shall be deemed to have been appointed by the constitution for the court where they were appointed and are working. |
| 2. ይህ አዋጅ ከመጽደቁ በፊት የተጀመሩ የዲሲፕሊንና ሌሎች ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት ታይተው ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡ | 2. Pending Disciplinary and other cases that started before the approval of this proclamation shall be considered and concluded according to this proclamation. |
| 3. በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መሠረተ-ሀሳብና ድንጋጌዎችን እስካልተቃረነ ድረስ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እስኪተኩ ድረስ በስራ ላይ ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች | 3. Without contravening the fundamental principles and provisions provided for in this Proclamation, effective regulations and directives shall continue their applicability until they are replaced by the rules and |

ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

**45. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፤

**46. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1) የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤
2) ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብ ለማስፈጸም የሚረዱ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፤
3) ዋና ጉባዔው በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት የሚያስችሉትን የአሰራር ስነ-ስርአትና የዲሲፕሊን ውስጠ-ደንቦችን ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

**47. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ታህሳስ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አርባ ምንጭ**

**ታህሳስ 5 ቀን 2016 ዓ.ም**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር**

regulations issued to implement this proclamation.

**45. Inapplicable Laws**

Any proclamation, regulation, directive or customary practice contrary to this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation;

**46. Power to issue Directive and Regulation**

1) The Main Judicial Administration Council may issue Regulations to enforce the Proclamation;
2) The Supreme Court may issue detail enforcement directive for the implementation of this Proclamation and the regulations to be issued in accordance with this Proclamation;
3) The Main Council may formulate rules of procedure and disciplinary rules for the fulfillment of the functions and responsibilities assigned to it by this Proclamation.

**47. Effective Date**

This proclamation shall be effective on the date of its ratification on December 15, 2023 approved by the Region Council.

**Done at Arba Minch**

**December 15, 2023**

**Tilahun Kebede**

**Chief Executive of South Ethiopia Region Sta**

| | |
|---|---|
| | |